**በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

ሐምሌ 22/2016 ዓም የዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት አስፈጻሚ ቦርድ የ2.556 ቢሊዮን SDR (ወደ 3.4 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ) የተራዘመ የብድር አገልግሎት አቅርቦትን ለኢትዮጵያ አጸደቀ። ይህም ውሳኔ የ766.75 ሚሊዮን SDR ወይም 1 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር አካባቢ የሚሆን ገንዘብ ክፍያ ወዲያውኑ እንዲለቀቅ የሚያስችል ይሆናል።

1. **ዐለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት የሚደግፈው የኢኮኖሚ ፕሮግራም አላማዎች ምንድን ናቸው?**
    - ፕሮግራሙ የመንግሥትን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ፣ የግሉን ዘርፍ እንቅስቃሴ የሚያነቃቃ ሁለገብ የፖሊሲ ፓኬጅን እንዲሁም የላቀ እና ይበልጥ አካታች የሆነ እድገትን የሚያበረታታውን የኢኮኖሚ ክፍትነት ይደግፋል።
    - ሌሎች የልማት አጋሮችም፤ በተለይም የዐለም ባንክ ከፍተኛ መጠን ያለውን የውጪ ገንዘብ በማቅረብ ላይ ሲሆኑ፤ ፕሮግራሙም በመካሄድ ላይ ያለው የእዳ ሪስትረክቸሪንግ በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ የሚያደርግ ማዕቀፍን ይሰጣል።
2. **ፕሮግራሙ መደበኛ የኢትዮጵያ ዜጎችን በመርዳት ረገድ ምን ሚና ይጫወታል?**
    - ኢንቨስትመንት እና እድገትን ወደኋላ የሚያስቀሩ መስተጓጎሎችን በማጥፋት እንዲሁም እንደ ጤና እና ትምህርት ላሉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ሕዝባዊ ወጪዎች ዘላቂነት ያለው የገንዘብ ሁኔታን በማቅረብ የመንግሥትን ፈጣን፣ አካታችና ዘላቂ ኢኮኖሚ የመፍጠር ፖሊሲ ይደግፋል።
    - ማሻሻያው ተጋላጭ በሆኑ ቤተሰቦች/አባዎራዎች ላይ የሚኖረውን ተጽእኖ ለማለዘብ ይቻል ዘንድ የማህበራዊ ሴፍቲ ኔቶችን ማጠናከርም የመንግሥት የማሻሻያ ፕሮግራም አንድ ወሳኝ ክፍለአካል ነው።
3. **ከፕሮግራሙ ቁልፍ አላማዎች አንዱ በገበያ ወደሚወሰን የምንዛሪ ዋጋ በመዞር ውጫዊ ኢሚዛናዊነቶችን ማረም ነው። ይህ እንደምን ኢትዮጵያን ይጠቅማል? እንዲሁም ተገላጭ ቤተሰቦች/አባዎራዎች ላይ ያለውስ ተጽእኖ ምንድነው?**
    - በገበያ ወደሚወሰን የምንዛሪ ዋጋ መዞር አሁን ያለውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እጥረት ያስታግሳል። የውጭ ንግድ ላኪዎች፣ ኢንቨስተሮች እና በኢትዮጵያ ለሚገኙ ወዳጆቻቸው እና ቤተሰቦቻቸው ገንዘብ የሚልኩ ሰዎች እንደሚያውቁት ይህ እነሱ ለሚልኩት ዶላር ተመጣጣኝ የሆነ ምንዛሪ ያስገኝላቸዋል። የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ከመጠን በላይ መጋሸብን፣ ኢንቨስትመንትን እና የኢትዮጵያን ልማት ወደኋላ የሚያስቀረውን እንዲሁም የተራዘመ የባላንስ ኦፍ ፔይመንት ተጋላጭነት የሚፈጥረውን ቁልፍ አንጻራዊ የዋጋ መስተጓጎል ያስቀራል።
    - የውጭ ምንዛሪ ዋጋውን ማስተካከል በአንዳንድ ከውጪ ሀገር የሚገቡ ሸቀጦችን ይበልጥ ውድ ያደርጋቸዋል። ይህ ውጤት በተለይ በተጋላጭ ሰዎች ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ ጫና ለማስታገስ፤ ድሆችን ኢላማ አድርገው የተቀረጹ ፕሮግራሞች የሚሰጡት ሽፋን እና ጥቅም ላይ የሚፈጠረው ጭማሪ እንዲሁም በውጭ ምንዛሪ ማሻሻው ተጽእኖ ለሚያድርባቸው እንደ ነዳጅ እና ማዳበሪያ ለመሳሰሉ ከውጪ የሚገቡ ቁልፍ ሸቀጦች የሚደረገው ጊዜያዊ ድጎማ፤ የገንዘብ ድርጅቱ በሚደግፈው ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የመጀመሪያ ዓመት ላይ የአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርቱን 1 ½% የሚሆን የወጪ ጥቅል በመጠቀም ይሸፈናል። ተገላጭ የሆኑ ቤተሰቦችን ኢላማ አድርገው ለሚሠሩ ፕሮግራሞች ወጪ የሚደረግ ገንዘብ በዘላቂነት እየጨመረ የሚሄድ ይሆናል።
4. **ኢትዮጵያ የፊስካል ዘለቄታዊነትን እንደምን ታጠናክራለች? ይህስ ደሆች ላይ የሚኖረው ተጽእኖ ምንድነው?**
    - የሕዝባዊ ወጪ ግቦቹን በተለይም ድሆችን የተመለከቱ ወጪዎቹን በዘላቂነት ለማሳካት፤ በሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ወደሚገኘው አማካኝ ደረጃ እስከሚጠጋ ድረስ መንግሥት ከታክስ የሚገኝ ገቢን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማሳደግ አቅዷል።

- ፕሮግራሙም የኤክሳይዝ ቴምብር እና ዘመናዊ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሥርዓትን በማስተዋወቅ፣ የፊስካል ዘለቄታዊነትን በማጠናከር ረገድ የሚያግዝ ሲሆን፤ በተጨማሪም ከምንዛሪ ዋጋ ማሻሻያው የሚገኙ አንዳንድ የግብር ገቢዎችም ይኖራሉ።
- ከፍ ያለ ገቢ መገኘቱ፤ ድሆችን ኢላማ ያደረጉ፣ ማህበራዊ እና የካፒታል ወጪዎች ለመሸፈን ያስችላል።

5. **ከፍተኛ የዋጋ ግሽበትን ለመከላከል ፕሮግራሙ ምን ያደርጋል?**
    - ፕሮግራሙ ከመጀመሩም በፊት መንግሥት የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰዱ ባለፉት ወራት የዋጋ ግሽበት እየቀነሰ መጥቷል። እነዚህም የዋጋ ግሽበት የሚያስከትለውን በሞኒታሪ ኤክስፓንሽን ወይም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚደረግ "ዳይሬክት አድቫንስ" የመንግሥትን የገንዘብ እጥረት የመሸፈን አሠራር መቀነስን፣ የብድር እድገት ላይ ጣሪያ መደንገግን እንዲሁም የፊስካል ወጪን መወሰንን ያካትታሉ።
    - ፕሮግራሙ በወለድ ምጣኔ ላይ የተመሠረተ እና በዋጋ መረጋጋት ላይ ያተኮረ ማዕቀፍ በማስተዋወቅ፤ የመንግሥትን የሞኒታሪ ፖሊሲ ማዕቀፍ የማዘመን ሥራ ይደግፋል። አዲስ የሞኒታሪ ፖሊሲ የወለድ ምጣኔ ማለትም የብሔራዊ ባንክ ምጣኔ እና የመጀመሪያዎቹ የሞኒታሪ ኦፕሬሽኖች ሐምሌ 4 ቀን 2016ዓም በሥራ ላይ ውለዋል። በተጨማሪም መንግሥት የ "ዳይሬክ አድቫንስ" አሠራርን ሙሉ በሙሉ የሚያስቀር ይሆናል።
    - የምንዛሪ ዋጋ ማሻሻያው በአንዳንድ ሸቀጦች ላይ የአንድ ጊዜ የዋጋ ጭማሪ ያስከትላል። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክም የዋጋ ግሽበቱ በፍጥነት እየቀነሰ ወደመሄዱ መመለሱን ለማረጋገጥ ሲባል የወለድ ምጣኔውን በማሳደግ ተጨማሪ የፖሊሲ እርምጃ መውሰድ ሊያስፈልገው ይችላል።

6. **ፕሮግራሙ የመልካም አስተዳደር እና የፀረ ሙስና አጀንዳዎችን ለማራመድ ምን እያደረገ ነው?**
    - መንግሥት ተቋማዊ ማዕቀፉን ለማጠናከር የሚሆኑ እርምጃዎችን እየወሰደ ነው። ፕሮግራሙ የሚደግፋቸው ቁልፍ እርምጃዎች የሚከተሉትን ይጨምራሉ፤
        - ፊስካል ነክ የሆኑ ማለትም በምንዛሪ ዋጋ እና በወለድ ምጣኔ መስተጓጎል አማካኝነት የተፈጠሩ በግልጽ የማይታዩ ግብሮችን እና ወጪዎችን በጀቱ ላይ በማካተት የፊስካል ግልጽነትን ማሻሻል፤ ለምሳሌ በነዳጅ እና በማዳበሪያ ላይ ግልጽ የሆኑ ድጎማዎችን በማድረግ።
        - የገንዘብ ሚኒስቴር ሪፖርቶችን በመደበኛነት ይፋ በማድረግ/በማሳተም የፊስካል ግልጽነትን ማሻሻል፤ 1) የበጀት ገቢን፣ ወጪን እና የፋይናንስ አፈጻጸምን የሚያሳይ ወርሃዊ ህትመት፤ 2) አፈጻጸምን እና ፖሊሲን የሚተነትን ሁለገብ የእኩለ ዓመት ግምገማ።
        - የመንግሥታዊውን ዘርፍ የገንዘብ አስተዳደር ሥርዓቶች ዲጂታል ማድረግ ወጪን በተሻለ ሁኔታ ለመከታተል እና ለመቆጣጠር እንዲሁም መረጃን በተሻለ ሁኔታ ለመሰብሰብ ይረዳል።
        - አዳዲስ የመንግሥት ኢንተርፕራይዝ አዋጅ እና ደንቦችን እና ጠንካራ የክትትል ተቋማትን በመጠቀም እንዲሁም፤ ቁልፍ የሆኑ የመንግሥት ኢንተርፕራይዞችን በተመለከተ በዐለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርቲንግ መመዘኛዎች (International Financial Reporting Standards) መሠረት ኦዲት የተደረጉ የሒሳብ መዛግብትን ይፋ በማድረግ/በማሳተም በመንግሥት ሥር ያሉ ኢንተርፕራይዞችን መልካም አስተዳደር እና ግልጽነት የማጠናከር ሥራን መቀጠል።
        - የዋጋ ግሽበትን የመቀነስ እና የፋይናንስ መረጋጋት የማምጣት ኃላፊነቱንት መወጣቱን ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን የሕግ ማዕቀፍ እና ነጻነት ማጠናከር።